ያዕቆብ ፡ ዮሴፍን ፡ ሦስት ፤ ቅስራ ፡ ኢያቄምን ፤ ኢያቄም ፡ እመቤታችንን፡ሦስት ፤ ጌታ፡፺ኛ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ አድርጎ ፡ ሱባዔ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሲቆጥር ፡ አበውም ፡ አብረው ፡ ተቈጥረዋል ፤ ሴትንስ ፡ ከወንድ ፡ አግብተው ፡ አይቈጥሩም ፡ ብሎ ፡ ባለፈው ፡ ያጸኗል ፤

፲ ፤ ወሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይወፅእ ፡ ወየኀልፍ ፤

የቀድሞው ፡ ሰማይ ፡ ጠፈር ፡ ያልፋል ፡ ይባላል ፤

ወሰማይ ፡ ሐዲስ ፡ ይትረአይ ፤

መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይሰጣል ፡ ይባላል ፡

ወኵሉ ፡ ኃይላተ ፡ ሰማያት፡ ያበርሁ ለዓለም ፡ ፯ተ ፡ ምክዕቢተ ፤

የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ የሚሆኑ ፡ ጻድቃን ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ ያበራሉ ፡ ይባላሉ ፤

፲፯ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ብዙኃን ፡ ሰንበታት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ኍልቍ ፡ ለዓለም ፡ በኂሩት ፡ ወበጽድቅ ፡ ይከውኑ ፤

ጌታ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በእውነት ፤ በቸርነት ፡ የሚደረጉ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ የትውልድ ፡ ሱባዔ ፡ ይሆናሉ ፤ አንድም ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ትከውን፡ ካልዕት ፡ ሰንበት ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እውነት ፡ ምሥጢር ፡ የሚገለጽባት ፡ ሁለተኛ ፡ የምትሆን ፡ ስምንተኛ ፡ የዘመን ፡ ሱባዔ ፡ ይሆናል ፤ ጌታ ፡ የተወለደ ፡ በ፭ሺህ ፡ ከ፭፻ ዘመን ፡ ነው ፤ ሰባቱን ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ሱባዔ ፤ ሰባቱን ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ሱባዔ ፤ እያልህ ፡ ቍጠር ፡ ከሽሑ ፡ ፫፻ ከሽሑ ፡ ፫፻ ፤ ዘመን ፡ እየነሣህ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሱባዔ ፡ አድርገው ፤ ፭ሺህ ፡ ከ፭፻ ዘመን ፡ ፯ ሱባዔ ሁኖ ፡ ፲፻ ፡ ይተርፋል ፤ ሕፁፁን ፡ ፫ መልቶ ፡ ፰ ፡ ሱባዔ ፡ እለ ፤ ወይትወሀብ ፡ ሰይፍ ፤ ለሐዋርያት ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣል ፤ እምእለ ፡ ይገፍዑ ፤ ነፍሳትን ፡ በሚበድሉ ፡ በአጋንንት ፡ እውነት ፡ ፍርድ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፤ ወይትሜጠዉ ፤ አጋንንት ፡ መናፍቃን ፡ በሐዋርያት ፡ እጅ ፡ ይወድቃሉ ፤ በተፍጻሜታ ፡ ያጠርዩ ፡ አብያተ ፤ ሐዋርያት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይዋጃሉ ፤ ወይትሐነጽ ፡ ቤት ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሠራል ፡ ወእምድኅረዝ ፡ በሰንበት ፡ ታስዕ ፡ ስምንቱ ፡ ሱባዔ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በ፱ነኛው ፡ ሱባዔ ፡ እውነተኛው ፡ ምሥጢር ፡

ወይትፌሥሑ ፡ መላእክት ፡ ዲበ ፡
ኃጕለ ፡ ዚአክሙ ፤
በሰማይም ፡ ያሉ ፡ መላእክት ፡
በእናንተ ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ ደስ ፡
ይላቸዋልና ፡ ይህ ፡ በደግነታ
ችሁ ፡ የታወቀ፡ ይሆንላችኋል ፤

፫ ፤ ምንተ ፡ ትግበሩ ፡ ሀለውክሙ ፡
ኃጥአን ፤
ኃጥአን ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡
አላችሁ ?
ወአይቴ ፡ ትጕይዩ ፡ በይእቲ፡ ዕለት ፡
እንተ ፡ ኮነኔ፤
ፍርድ ፡ በሚሰጥባት ፡ በዚያች ፡
ቀንስ ፡ ወዴት ፡ ትሸሻላችሁ ?
ሶበ ፡ ትሰምዑ ፡ ቃለ ፡ ጸሎቶሙ ፡
ለጻድቃን ፤
የጻድቃንን ፣ የጸሎታቸውን ፡
ዋጋ፡ ንው ፡ ኀቤየ ፡ ሲላቸው ፡
በምትሰሙበት ፡ ጊዜ፡ ወዴት ፡
ትሸሻላችሁ ?
ወአንትሙ ፡ ኢትከውኑ ፡ ከማሆሙ ፡
አላ ፡ ሰማዕተ ፡ ይከውን ዲቤክሙ ፡
ዝንቱ ፡ ነገር ፤
ይህ፡ መከራው ፡ ምስክር ፡ የሚ
ሆንባችሁ ፡ ኀጥአን ፡ እንደ ፡ እነር
ሳቸው ፡ አትሆኑም ፤ አንድም ፡
አላ ፡ ሰማዕተ ፡ ይከውን ፡ ዲቤ
ክሙ ፣ ይህ ፡ ኃጢአቱ ፡ ምስክር ፡
ይሆንባችኋል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡
ጻድቃን ፡ አትሆኑም ፤
እስመ ፡ ሱቱፋነ ፡ ኮንክሙ ፡ ለኀጥአን ፤
እኩሌቶቹ ፡ ኃጥአን ፡ እንደ ፡
እኩሌቶቹ ፡ ኃጥአን ፡ ሆናችሁ
ይላቸዋል ፣ በመከራው ፡ ተባባ
ሪዎች ፡ ሆናችሁ ፤

፭ ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ትበጽሕ ፡
ጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኀበ ፡ እግዚአብ
ሔር ፤
በእነዚያም ፡ ወራቶች ፡ የቅዱሳን ፡
ልመናቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር፡
ትደርሳለች ፡
ወለክሙ ፡ ይበጽሕ ፡ መዋዕለ ፡ ኮነ
ኔክሙ ፤
በእናንተ ፡ ግን ፡ የሚፈረድባ
ችሁ፡ ወራት ፡ ይደርስባችኋል ፤

፮ ፤ ወይትነበብ ፡ ኵሉ ፡ ነገረ ፡
ዓመፃክሙ ፡ ቅድመ ፡ ዓቢይ ፡ ወቅ
ዱስ ፤
በግፋችሁ፡ የሠራችሁት ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ በከበረና ፡ በገነነ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ይነበባል ፤
ወይትኀፈር ፡ ገጽክሙ ፤ ወይትገደፍ ፡
ኵሉ፡ ተግባርክሙ ፡ ዘጸንዐ ፡ በዓመፃ፤
ፊታችሁም ፡ በመከራው ፡ ያፍ
ራል ፤ በግፍ ፡ የጸና ፡ ሥራች
ሁም ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል፤

፯ ፤ አሌ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥአን ፡ እለ ፡
ማእከለ ፡ ባሕር ፡ ወዲበ ፡ የብስ ፤
በባሕርና ፡ በደሴት ፡ የምትኖሩ
ወዮላችሁ ፤ በደሴት ፡ ያሉ ፡
ሰዎች ፡ ይታበያሉና ፤

ትትወደይ ፡ መንፈሶሙ ፡ ውስተ ፡
እቶነ ፡ እሳት ፤
ነፍሳቸው ፡ በገሃነም ፡ ትወድ
ቃለች ፤

፲፯ ፤ መሐልኩ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥአን
ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤
ተራራ ፡ በባሕርዩ ፡ ተገኝቶ ፡
እንዳልነበረ ፤ ወኢይከውን ፤ እን
ግዲህም ፡ መገዛት ፡ እንደሌለ
በት ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፤
ወኢወግር ፡ ለብእሲት አመተ ፤
ኮረብታም፡ ለሴት ፡ ተገኝቶ ፡ እን
ዳይደለች ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋ
ለሁ ፤

፲፰ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአትኒ ፡ ኢተፈ
ነወት ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ተራራ ፡ ኮረብታ ፡ በባሕርያ
ቸው ፡ መገዛት ፡ እንደሌለባቸው፡
ኃጢአትም ፡ የባሕርይ ፡ ሁና ፡
አልተፈጠረችም ፤
አላ ፡ሰብእ ፡ እምርእሶሙ ፡ ፈጠርዋ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ከልቦናቸው፡
አንቅተው ፡ ሠሯት ፡ እንጂ ፤
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፡ እለ
ገብርዋ ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ለፍጹም ፡
ጥፋት ፡ ይሆናሉ ፤ አንድም ፡
ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤ ዓበይት ፡
ነቢያት ፡ አሪትን ፤ ነዋሪት ፤
ቀዋሚት፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡
እንዳላስተማሩ ፤
ወኢወግር ፤ ለብእሲት ፡ አመተ፤
ደቂቅ ፡ ነቢያትም ፡ አምሳል ፡
መርገፍ፡ የምትሆን ፡ አሪትን ፡
ነዋሪት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡
እንዳላስተማሩ ፡ ምዬ ፡ እነግራ
ችኋለሁ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአት ፡
ኢተፈነወት ፡ አሁን ፡ እንደተ
ናገርሁት ፡ ኃጢአትም ፡ ነዋሪት
ሕግ ፡ ሁና ፡ አልተሠራችም ፤
አላ ፡ ሰብእ ፡ እምርእሶሙ ፡
ፈጠርዋ ፤ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡
ልብ ወለድ ፡ አንቅተው ፡
ቀዋሚት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡
አስተማሯት ፡ እንጂ ፡
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፤
ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ለጽኑ ፡ መር
ገም ፡ ይሆናሉ፤ (ሑሩ ፡ እምኔየ ፡
ይባላሉ ፤)

፲፱ ፤ ወምክነት ፡ ለብእሲት ፡ ኢተ
ውህበ ፤
ለሴት፡ ምክነት፡ አልተሰጣትም፤
አላ ፡ በግብረ ፡ እዴሃ ፡ ትመውት ፡
ዘእንበለ ፡ ውሉድ ፤

፲፫ ፡ ወሰበ ፡ ይወዲ ፡ ቃሉ ፡ ዲቤ
ከሙ ፡
የመዓቱን ፡ ቃል ፡ ወደእናንተ ፡ ባመጣው ፡ ጊዜ ፡
አኮኑ ፡ ትትማህከው ፡ ወትፈርሁ ፡ ትደ
ነግፁ ፡
ትወድቁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የምት
ፈሩ ፡ የምትደነግጡ ፡ የምትወ
ድቁ ፡ አይደለምን ?
ወኮሉሙ ፡ ብርሃናት ፡ ይትማህ
ከዉ ፡ ወይትሀወኩ ፡ በፍርሀት ፡
ዓቢይ ፡
ብርሃኖችስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡ ፍርሀት ፡ ተይዘው ፡ የሚፈሩ ፡ የሚደነግጡ ፡ አይደለምን ፡
፲፬ ፡ ወኮላ ፡ ምድር ፡ ትትማህከው ፡
በፍርሀት ፡ ዓቢይ ፡
ትፈርህ ፡ ትደነግፅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ምድርስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡ ፍርሀት ፡ ተይዛ ፡ የምትን ቀጠቀጥ ፡ አይደለምን፤
ወትርዕድ ፡
ለኀልፈት ፡ ትቀርባለች ፡
ወትጓጕፅ ፡
ለኀልፈት ፡ ትቸኩላለች ፡
፲፭ ፡ ወኮሉሙ ፡ መላእክት ፡ ይፌ
ጽሙ ፡ ትእዛዞሙ ፡
መላእክትም ፡ ሁሉ ፡ የታዘዙ
ትን ፡ ይፈጽማሉ ፡
ወይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይትኀብኡ ፡
እምቅድመ ፡ ዓቢየ ፡ ስብሐት ፡
ከክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ ፊት
ሊሰወሩ ፡ ይወዳሉ ፡
፲፮ ፡ ወይርዕዱ ፡ ደቂቀ ፡ ምድር ፡
ወይትሀወኩ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ ይርዳሉ ፡ (ይንቀጠቀጣሉ) ፡ ይታ
ወካሉ ፡
ወአንትሙ ፡ ኃጥአን ፡ ርጉማን ፡ ለዓ
ለም ፡
እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ ለዘለዓ
ለሙ ፡ የተረገማችሁ ፡ ናችሁ ፡
ወአልብክሙ ፡ ሰላም ፡
ፍቅር ፡ አንድነትም፡ የላችሁም ፡
፲፯ ፡ ኢትፍርሁ ፡ አንትሙ ፡ ነፍ
ሳተ ፡ ጻድቃን ፡
እናንተ ፡ የጻድቃን ፡ ሰውነቶች
አትፍሩ ፡
ወተሰፈዉ ፡ እለ ፡ ሞትክሙ ፡ በጽ
ድቅ ፡
በእውነት ፡ ነገርም ፡ የሞታችሁ
ሰዎች ፡ ዋጋችሁን ፡ እንድታገኙ
ተስፋ ፡ አድርጉ ፡
፲፰ ፡ ወኢትኅዝኑ ፡ እስመ ፡ ወረደት ፡
ነፍስክሙ ፡ ውስተ ፡ ዓቢይ፡ ምን
ዳቤ ፡
ሰውነታችሁ ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡
ሳለች ፡

ወለእለ ፡ ይጸልእዎነ ፡ አትሐትነ ፡ ክሣደነ ፨
ለሚጠሉንም ፡ ለጠላቶቻችን ፡ እንገታችንን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደ ረግን ፨
ወኢመሐሩነ ፨
እነርሱ ፡ ግን ፡ አልራሩልንም ፡ አትበሏቸው ፨
፲፰ ፨ ወፈቀድነ ፡ ንሑር ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ንንፍጽ ፡ ወናዕርፍ ፨
ከእነርሱ ፡ ሸሽተን ፡ ከመከራው፡ ልናርፍ ፡ ወደድን፨
ወኢረከብነ ፡ ኀበ ፡ ንጕይይ ፡ ወንድ ኀን ፡ እምኔሆሙ ፨
ከነሱም ፡ ሸሽተን ፡ የምንድንበት ቦታ ፡ አላገኘንም፨
፲፱ ፨ ወሰከይናሆሙ ፡ ኀበ ፡ መላእ ክት ፡ በምንዳቤነ ፨
በመከራችን ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻ ችነን ፡ ከአለቆች ፡ ከሰስናቸው ፨
አንድም ፡ ከመላእክት ፡ ዘንድ ፡ ከሰስናቸው ፡
ወጸራሕነ ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ይበልዑነ ፨
ገንዘባችነን ፡ በሚበሉብን ፡ በጠ ላቶቻችን ፡ ወደ ፡ አለቆች ፡ ጮኽን ፨ አንድም ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡ ጮኽን ፨ አንድም፡ ወሰከይናሆሙ ፡ ልመናችንን ፡ አድርሱልን ፡ ብለን ፡ ጻድቃንን፡ ወደ መላእክት ፡ አካሰስናቸው ፨
ወጸራሕነ ፨ በሚበድሉን ፡ በጠላ ቶቻችን ፡ ጩኸታችንን ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡ አድርሱልን ፡ ብለን፡ ለጻድቃን ፡ ጮኽነ ፨
ወጽራሐ ፡ ዚአነ ፡ ኢይርእዩ ወኢይ ፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ቃለነ ፨
ኢይሬእዩ ፡ ሲል ፡ ነው ፨ ልመና ችንን ፡ ጻድቃን ፡ መላእክት ፡ አይሰሙም ፨
፳ ፨ ወይረድዕዎሙ ፡ ለእለ ፡ የሀይ ዱነ ፡ ወይበልዑነ ፨
ለሚቀሙን ፡ ገንዘባችንንም ፡ የሚበሉብንን ፨
ወለእለ ፡ አውኀዱነ ፨
ያሳነሱንን ፨
ወየኀብኡ ፡ ግፍዖሙ ፨
ግፋቸውንም ፡ ይሰውሩላቸዋል እንጂ ፨
ወኢያወጽኡ ፡ እምኔነ ፡ አርዑቶሙ ፨
አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፋል ንም ፨
እለ ፡ ይበልዑነ ፨
ገንዘባችንን፡የሚበሉብንን፡ሰዎች፡ አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፋል ንም ፨

እስመ ፡ እምነ ፡ መላእክት ፡ ይት
ኀሠሥ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤክሙ ፤
ወደ ፡ መላእክት ፡ ከመካሰሳችሁ
የተነሣ ፤እንድም ፡ መላእክትን ፡
አድርሱልን ፡ ከማለታችሁ ፡ የተ
ነሣ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱም ፡ አን
ዱም ፡ መከራችሁን ፡ ይመረም
ራሉ ፤
ወእምኵሎሙ ፡ እለ ፡ አርድዕምሙ ፡
ለእለ ፡ የኀይዱክሙ ፤
የሚቀሙችሁን ፡ ሠራዊቱን ፡
ከሚረዱ ፡ ከነገሥታቱ ፡ የተነሣ ፤
አንድም ፡ የሚቀሙችሁ ፡ ነገሥ
ታቱን ፡ ከሚረዱ ፡ ከሠራዊቱ ፡
የተነሣ፤
፭፮ ፤ ተሰፈዉ ፡ ወኢትኀድጉ ፡
ተስፋክሙ ፡ እስመ ፡ ትከውን ፡
ለክሙ ፡ ፍሥሓ ፡ ዓባይ ፡ ከመ ፡
መላእክት ፡ በሰማይ ፤
እንደ ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡
ታደርጓት ፡ ዘንድ ፡ ያላችሁን ፡
ብዙ ፡ ደስታ፡ እንድታደርጉ ፡ ተስፋ፡
አድርጉ ፤ አለኝታችሁን ፡
አትተዉ ፡፡
እንተ ፡ ሐለወክሙ ፡ ትግበሩ ፡ አከ ፡
ከመ ፡ ትትኀብኡ ፡ ሀለወክሙ ፡
በዕለተ ፡ ኵነኔ ፡ ዓባይ ፤
ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን፡
ትሰወሩ ፡ ዘንድ ፡ ያላችሁ ፡
አይደለም ?

፭፯ ፤ ወኢትትረከቡ ፡ ከመ ፡ኃጥአን፤
እንደ ፡ ኃጥአንም ፡ ሁናችሁ ፡
አትገኙ ፤
ወኵነኔ ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፡ ትከውን ፡
እምኔክሙ ፡ ለኵሉ ፡ ትውልደ ፡
ዓለም ፤
እናንተን ፡ ከመበደላቸው ፡ የተ
ነሣ ፤ አንድም ፡ ከእናንተ ፡ ተለ
ይተው ፡ በኃጥአን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡
የምትኖር ፡ ፍርድ ፡ ትደረጋለች ፤
አንድም ፤ ወጽርሐ ፡ ዚአክሙ ፡
ኵነኔ ፡ ጽርሑ ፤
በኃጥአን ፡ መቻያ ፡ የሚሆን ፡
ጸሎታችሁን ፡ ጩኹ ፤ ወያስተ
ርኢ ፡ ለክሙ ፤ በረድኤት ፡ ይገ
ለጽላችኋል ፤
፭፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኢትፍርሁ ፡ ጻድቃን፡
ሶበ ፡ ትሬእይዎሙ ፡ ለኃጥአን ፡
ይጸንዑ ፡ ወይዴሉዉ ፡ በፍትወቶሙ ፤
ጻድቃን ፡ ኃጥአንን ፡ ጸንተው ፤
በፈቃዳቸው ፡ ተዘጋጅተው ፤
ባያችኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አትፍሩ ፤
፭፱ ፤ ወኢትኩኑ ፡ ሱቱፋነ ፡ ምስሌ
ሆሙ ፡ አላ ፡ ረሐቁ ፡ እምግፍዐ ፡
ዚአሆሙ ፤
እነርሱ ፡ ከሚሠሩት ፡ ግፍ ፡
ራቁ ፡ እንጂ ፤ ከእነርሱ ፡ ጋራ፡
የተባበራችሁ ፡ አትሁኑ ፤

፲፱ ፤ ወይከውን ፡ መቅሠፍት ፡ ዓቢይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ጽኑ ፡ መቅሠፍትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይደረጋል ፤
ወትትሐፀብ ፡ ምድር ፡ እምኵሉ ፡ ሙስና ፤
ምድርም ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ትነጻለች ፤
፳ ፤ ወይእዜኒ ፡ አይድዕ ፡ ለወልድከ ፡ ላሜህ ፤
አሁንም ፡ ለልጅህ ፡ ለላሜህ ፡ ንገረው ፤
እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ ወልዱ ፡ ውእቱ፡ በጽድቅ ፤
ይህ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ በእውነት ፡ የእርሱ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ፡ ንገረው ፤
ወጸውዕ ፡ ስሞ ፡ ኖኅ ፡ እስመ፡ ውእቱ፡ ይከውን ፡ ለከሙ ፡ ተረፈ ፤
ኖኅ ፡ ማለት ፡ ተረፍ ፤ ትፍሥሕት ፤ ዕረፍት ፡ ማለት ፡ ነው፤ እርሱ ፡ ከጥፋት፡ የቀረ ፡ ይሆንላችኋልና ፡ ስሙንም ፡ ኖኅ ብለህ ፡ ጥራው ፤
ወውእቱ ፡ ወደቂቁ ፡ ይድኅኑ እሙስና ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምኵሉ ፡ ኃጢአት ፤
በእርሱ ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ ትጨረስ ፡ ዘንድ ፡ ካላት ፡ በደል ፡ ሁሉና ፡ ከኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከምትመጣ ፡ ጥፋት ፡ ልጆቹና ፡ እርሱ ፡ ይድናሉ ፤
ወእምኵሉ ፡ ዓመፃ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ትትፌጸም ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በመዋዕሊሁ ፤
በእርሱ ፡ ዘመን ፡ ከምትመጣ ፡ ጥፋት ፡ ልጆቹና ፡ እርሱ ፡ ይድናሉ ፤
ወእምድኅረዝ ፡ ትከውን ፡ ዓመፃ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእንተ ፡ ተፈጸመት ፡ ቀዳሚ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ከአለፈችው ፡ ኃጢአት ፡ ይልቅ ፡ ፈጽማ ፡ የምትበልጥ ፡ ግፍ ፡ ትደረጋለች ፤ ሰብአ ፡ ትካት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንውጋ ፡ አላሉም ፤ ሰብአ ፡ ሰናዖር ፡ ግን እግዚአብሔርን ፡ እንውጋ ፡ ብለዋልና ፤ አንድም ፡ ሰው ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፤ ኃጢአትም ፡ ይበዛልና ፤ አንድም ፡ ሰብአ ፡ ትካት፡ የጠፉት ፡ ሕግ ፡ ተሠርቶላቸው ፡ ከሕግ ፡ ወጥተው ፡ የበደሉ ፤ አብነት ፡ ባይኖራቸው ፡ ነው ፤ እሊህ ፡ ሰብአ ፡ ሰናዖር ፡ ግን ፡ሕግ ፡ ተሠርቶላቸው ፤ ከሕግ ፡ ወጥተው ፤ የጠፉት ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ አብነት ፤ እያሏቸው ፡ ነውና ፤

፲፯ ፤ ወየሐውሩ ፡ እሙንቱሂ ፡ በኀበ ተጽሕፈ ፡ ሎሙ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፤

እነርሱም ፡ በተጻፈላቸው ፡ ዘመኖችና ፡ ቀኖች ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ አንድም ፡ በኀበ ፡ ኢተጽሕፈ ፡ ሎሙ ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ቀን ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ኑራችሁ ፡ ትመጣላችሁ ፣ ተብሎ ፡ ወዳልተጻፈላቸው ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ገነት ፣ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፣ ጻድቃን ፡ ይሔዳሉ ።

ተፈጸመ ፡ ራእየ ፡ ሄኖክ ፡ ነቢይ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፤

ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ነቢዩ ፡ ሄኖክ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ተፈጸመ ።

ጉባዔ ፡ ሄኖክ ፡ ፴ ፡ ወ፩ዱ ፡ ዘኍለቄ ፣

ሄኖክ ፡ የቆጠረው ፡ ሠላሳ ፡ አንዱ ፡ ጉባኤ ፤

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እነሣሥት ፡ ለአስጀመረን ፣ እተጋግት ፡ ለአስፈጸመን ፡

ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፤

አሜን ።